በሕብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፤
ጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ ።

የወንጀል ይግባኝ መ.ቁ. 4/71
ኅዳር 7 ቀን 1772 ዓ. ም.

ዳኞች ፦
1.
2.
3.
4.
5.

ይግባኝ ባዮች ፦
1/ አለቃ ወ. ሃ. ሰ.
2/ ቢ. ተ.

መልስ ሰጭ ፦ ዓቃቤ ሕግ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል ።

## ው ሳ ኔ

ለዚህ ይግባኝ መነሻ የሆነው አንደኛው ይግባኝ ባይ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 20 የተጻፈውን ድንጋጌ ተላልፎ አቶ ኃ. ፀ.ን በማስገደሉ ለምር መራ ታስሮ በነበረበት ጊዜና ከወጣም በኋላ ጥፋቱ እንዳይደረስበትና በፍርድ እንዳይቀጣ ዳኞችና መርማሪዎች በሥራ ግዴታቸው ማድረግ የማይገባቸውን እን ዳያደርጉ ወይም እንዲያደርጉ በማሰብ ከአምስት ሺህ ብር በላይ ጉቦ ሰጥቷል ፤ እንዲሁም ሁለተኛው ይግባኝ ባይ እላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ተላልፎ የአንደ ኛው ይግባኝ ባይ አባሪ በመሆን እሥር ቤት አብሮ በነበረበት ጊዜ ከአንደኛው ይግባኝ ባይ ሁለት ሺህ ብር ተቀብሎ ጉዳዩን ለያዘው መርማሪ ለሻምበል ባሻ ገ.ሥ ሰጥቷል ፣ ከእሥር ቤት ከወጣም በኋላ ጉቦ ለመስጠት የወሰደውን ሌላ ሁለት ሺህ ብር ለራሱ ጥቅም አውሏል ተብለው በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት ተከሣሾቹን በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኞች አድርጐ አንደኛው ተከሣሽ በአስር ዓመት ጽኑ እሥራት ፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ደግሞ በስድስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ መስከረም 7 ቀን 1972 ዓ. ም. በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 203/71 የሰጠውን ፍርድ በመ ቃወም ነው ።

የይግባኝ ባዮቹ ጠበቃ ደንበኞቹ የተነገረባቸውን ወንጀል ለመፈጸማቸው አስተማማኝ በሆነ የሰስተኛ ሰው አስረጂነት አልተረጋገጠባቸውም ፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በድምጽ ብልጫ የሰጠው ፍርድ መሠረት ያደረገው ተከሣሾቹ ለፖሊስ ሰጥተዋል የተባለውን የእምነት ቃል ነው ፣ የእምነቱ ቃል ግን በፈቃደኛነት ሳይ ሆን በማስገደድ በድብደባ የተገኘ ነው ፤ ተከሣሾቹ በምርመራ በነበሩበት ጊዜ ከ ባድ ድብደባና ከፍተኛ ስቃይ የደረሰባቸው መሆኑን በቆጠሯቸው መከላከያ ምስ ክሮች በሚገባ አስረድተዋል ፣ ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጥ ተውታል ተብሎ የቀረበለትን የእምነት ቃል በፈቃደኛነት ሳይሆን በማስገደድ የተገኘ መሆኑን በተቃራኒ ማስረጃ እያረጋገጥን ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው በማይገባው ነው ፣ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ የተሰጠውን

ፍርድ ሸሮ በአንስተኛ ድምጽ የተሰጠውን የውሳኔ አስተያየት በመደገፍ ይግባኝ ባዮቹን በነጻ ያሰናብትልኝ ሲል ጠይቋል ።

ክርክሩን በዚህ ፍርድ ቤት በመልስ ሰጭነት የሚመራው ዐቃቤ ሕግም በበኩሉ ጥቅምት 29 ቀን 1972 ዓ. ም. በተጻፈ ሶስት ገጽ የመልስ ማመልከቻ ፣ ይግባኝ ባዮች በተከሰሱበት ወንጀል በጣቢያ ከሰጡት የእምነት ቃል ሌላ የቀረበባቸው ግዙፍ ማስረጃ የለም ፣ በምርመራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ አ ራት ቀን በተከታታይ እንደተደበደቡና ቆስለውም እንደነበረ የመከላከያ ምስክሮ ቻቸው አረጋግጠውላቸዋል ፣ በዚህም ምክንያት በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠው የእ ምነት ቃል ያላንዳች ማስገደድ በፈቃደኛነት የተገኘ ነው ለማለት አይቻልም ፣ ይግባኝ ባዮቹ ወንጀሉን ለመፈጸማቸው በአጥጋቢ ማስረጃ አልተረጋገጠባቸውም ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአነስተኛ ድምጽ የተሰጠውን የውሳኔ አስተ ያየት ደግፎ ይግባኝ ባዮቹ በነፃ ቢለቀቁ አንቃወምም ሲል አሳስቧል ።

ይግባኝ ባዮቹ አስቀድመው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተከራከሩት ፣ አሁንም በይግባኝ ደረጃ በዚህ ፍርድ ቤት አጥብቀው የሚከራከሩት በክስ አቤቱታው ላይ የተነገረባቸውን ወንጀል መፈጸማቸውን በመካድ ነው ። ዐቃቤ ሕጉ ክሱን ለማ ስረዳት ያቀረበው ማስረጃ ተከሣሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጡ የተባሉትን የእምነት ቃልና የእምነት ቃሉን ሲሰጡ ነበሩ የተባሉ አስረጂዎችን ብቻ ነው ።

ተከሣሾቹ የእምነቱን ቃል በፖሊስ ጣቢያ መስጠታቸውን ያልካዱትና የማይክዱት ነገር ነው ። የእነርሱ ክርክር ወንጀሉን መፈጸማችንን ያመንነው በተከታታይ ለአራት ቀናት ስለተደበደብን የደረሰብንን ስቃይ መቋቋም ባለ መቻላችን ነው የሚል ነው ። በምርመራ በነበሩበት ጊዜ ተከሣሾቹ የድብ ደባ ተግባር የተፈጸመባቸው ለመሆኑ መከላከያ አስረጂዎች አቅርበው አረጋ ግጠዋል ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሣሾቹን በድምጽ ብልጫ ጥፋተኞች ያደረጋ ቸው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተገኘውን የተከሣሾቹን የእምነት ቃል ሐቀኛና ብቁ ነው በማለት ነው ። በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠው የእምነት ቃል ብቁና ሐቀኛ መሆኑን ለማሳመንም የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በብዙ አንጻሮች አጠያያቂ የሆኑ የትችት ነጥቦች ሠፍሮበት ይታያል ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ « በድብደባ ለነ ፍስ አድን የሚሠነዘር የፈጠራ ቃል እንደመኖሩ መጠን በድብደባም አማካኝነት የሚወጣ ሐቅ እንዳለም መዘንጋት አይገባም » ይላል ። ይህ አስተያየት በምር መራ ደረጃ የሚፈጸም ማባበልን ፤ ማስፈራራትንና የኃይል ተግባርን ተገቢ ነው ብሎ የሚያጸድቅ ነው ። በምርመራ ጊዜ አንድ መግለጫ ለማግኘት ወይም ጥፋ ትን ለማሳመን የሚፈጸም የኃይል ተግባር በሕግ የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ (ወ. መ. ሕ. ቁጥር 417 እና ልዩ ወ. መ. ሐ ቁጥር21) መሆኑ ቀረና ፣ የእምነት ቃልም አጠራጣሪነቱ ተረሳና ፣ ፍርድ ቤት የሚሠራው በሕግ ፣ ሕግም የተደነገገው የኃይል ተግባርን ለመቋቋም መሆኑ ተረሳና ድብደባ መልካም ነው ፣ ሐቁን ያወጣል የሚል ትችት ሰብአዊ መብት ይከበርበታል ፣ የተበደለም ይካስበታል ፣ የበደለም ይቀጣበ በታል ተብሎ አደራ ከተጣለበት የፍትሕና ርትዕ አደባባይ መሠንዘሩ እጅግ አሳ ዛኝ ነው ። እርግጥ በማባበል፣ በማስፈራራትና የኃይል ተግባር በመጠቀም አንዳንድ ጊዜ የተዳፈነ ሐቅ ይፋ ሊወጣ ይችላል ። መታወቅ ያለበት ቁም ነገር ግን የወንጀል ተግባር ፈጽሞ ይሆናል ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ሁሉ ወንጀለኛ አለመሆኑ ነው ። ሐቅን ለማግኘት ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘው ሁሉ የኃይል ተግባር የሚፈ ጸምበት ከሆነ ደግሞ ንጹኃን ጭምር መበደላቸውና መጐዳታቸው አይቀርም ። ተጠርጣሪው በእርግጥ ወንጀለኛ ቢሆን እንኳ ፣ የኃይል ተግባር ከተፈጸመበት ሽብ

ርና ጭንቀት ስለሚያደርበት የሚሰጠው የእምነት ቃል ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ
ትክክለኛ ፣ ሐቀኛና አስተማማኝ ሊሆን አይችልም ። ሕግም ሆነ ትክክለኛ የዳኝ
ነት አስተያየት እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ የሚያወግዙት ንጹኃን አላግባብ እንዳይ
በደሉና ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ ባልፈጸሙት ተግባር ራሳቸውን እንዳይወ
ነጅሉ ነው ። የሕጉ ምርጫ ንጹኃን አላግባብ ከሚበደሉ አጥፊው ቢያመልጥ ይሻ
ላል ነው ። ድብደባ ሕገወጥ አድራጎት በመሆኑ ፣ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ የእ
ምነት ቃልም ሕጋዊ ሊሆን አይችልም ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ትችቱን በመ
ቀጠል « የዓለም ሕዝብ በሥልጣኔ እየተራመደ እንደመሄዱ መጠን የወንጀል አፈ
ጻጸሙ ዘዴም ያን ያህል የረቀቀ ስለሆነ ፣ እውነቱን ለማግኘት ብዙ ብልሃት የማድ
ድረጉ ጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል » ይላል ። እርግጥ የዕድገት ደረጃ ከፍ እያለ ፣
ሥልጣኔም እየገፋ ሲሄድ የወንጀል ተግባራትም በረቀቀ ዘዴ እንደሚፈጸሙ አያ
ከራክርም ። በአንጻሩ ሕግን ፣ ሰላምንና ጸጥታን በሚያስከብረው ክፍል በኩልም
ለመፈጸም የታቀደ ወንጀልን ለማክሸፍ ወይም የተፈጸመ ወንጀልን ፈልፍሎ ይፋ
ለማውጣትና አጥፊውንም ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት ያስፈ
ልጋል ። እስከዚህ ድረስ በድምጽ ብልጫ ከተሰጠው ውሳኔ የተለየ አስተያየት የለ
ንም ። መቸም ቢሆን ግን ድብደባ ሥልጣኔ ያስገኘው የወንጀል ተግባር ማክሸፊያ
ወይም ማጋለጫ ልዩ ጥበብ ፣ የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት ነው አንልም ። ድብደባ አሪ
ታዊ እንጂ ሥልጣኔ ያስገኘው ዘመናዊ የምርመራ ሥልት አለመሆኑ ለማንም የታ
ወቀና መታወቅም ያለበት ነገር ነው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ግን ሊያሳምነን
የሞከረው ድብደባ ሐቁን ለማውጣት ሥልጣኔ ያስገኘው የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት
መሆኑን ነው ። ትችቱ ድብደባ የተፈቀደ ዘዴና ብልሃት መሆኑን ለማሳመን ባደረ
ገው ሙከራ ብቻ ተወስኖ አልቀረም ። በድብደባ የተገኘ የእምነት ቃል በሚቀር
ብበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች በተለይም በሶሺያሊስት አገር ያሉ ፍርድ ቤቶች ምን ማድ
ረግ እንዳለበባቸው ተግባራዊ መሠረት ይጥልላቸዋል ። ይህንንም አሳብ «የሶሻያሊ
ስት አገር ፍርድ ቤቶች ዓይነተኛ ዓላማም የመንግሥት አካል እንደመሆናቸው መ
ጠን ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ መሻት ስለሆነ በፖሊስ በኩል የሚቀርበውን
ቃለ ምርመራ በጥሞና አጥንተው በጉዳዩ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ነው እንጂ
ያለባቸው ፣ አንዳንድ ጥቃቅን የሥርዓተ ሕግ ፎርማሊቲ አልተሟላም ተብሎ ብዙ
ድካም የተወሰደበትን ቃለ ምርመራ ውድቅ ማድረግ ተገቢ አሠራር ነው ብለን
እናምንበትም » በማለት ገልጦታል ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በአንድ በኩል
ፍርድ ቤቶች ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ መሻት ነው ይልና በሌላ በኩል ደግሞ
ብዙ የተደከመበትን የምርመራ ውጤት ውድቅ ማድረግ የለባቸውም ይላል ። በፖ
ሊስ ምርመራ « ተጣርቶ » የቀረበላቸውን ሁሉ ውድቅ ሳያደርጉ እንዳለ መቀበል
ካለባቸው ፍርድ ቤቶች ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ እንዴት አድርገው መሻት
እንደሚችሉ በፍጹም ሊገባን አልቻለም ። በምርመራ ተገኘ የተባለውን ውጤት
የሕግን ፎርማሊቲ ሳይከተሉ ራሳቸው ሳይመራመሩና ሳያመዛዝኑ እንዳለ ይቀበ
ሉት ከተባለ በጥሞና የሚያጤኑት ምኑን እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው ። የድብ
ደባ ተግባር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ ተዘንግቶ የአንድ ተጠርጣሪ የእም
ነት ቃል በድብደባም ቢገኝ ድብደባ ክብደት የማይሰጠው የሕግ ፎርማሊቲ ስለሆ
ነና ብዙ ድካምም ስለተወሰደበት ሀቅነቱን እትጠራጠሩ ከተባለ የሕግ እውታር
መዘርጋትና የፍርድ ቤቶች መኖር በፍጹም አያስፈልግም ማለት ነው ። አንድ ተከ
ሳሽ ፍርድ ቤት የሚቀርበው ተመሳክሮና ተነጣጥሮ ፣ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩንና የቀ
ረበለትን ማስረጃ በገለልተኛነት አይቶለትና መዝኖለት ሐቀኛው ፍሬ ነገር ነጥሮ
እንዲወጣና ተገቢውን ዳኝነት እንዲያገኝ ነው ። በድምጽ ብልጫ እንደተሰጠው
ውሳኔ ከሆነ ግን የፍርድ ቤት ተግባር ጉዳዩን ማበጠርና እውነቱን ማንጠር ሳይሆን

በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበለትን ማስረጃ ሐቀኛነቱን ሳይጠራጠር አሜን ብሎ መቀበል ነው ። የፍርድ ቤት ተግባር ለዐቃቤ ሕጉ ማስረጃ ቡራኬ መስጠት ብቻ ከሆነ ደግሞ የፍርድ ቤት መኖርና የተከሰሰም ሰው ፍርድ ቤት መቅረቡ ባላስፈለገም ነበር ። በድምጽ ብልጫ የተሰጠው ውሳኔም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያጸድቀው ይህንኑ አስተያየት ይመስላል ።

አንደኛው ይግባኝ ባይ ኃ. ፀ.ን አስገድሏል ተብሎ በከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ ከተመረበረ በኋላ ኅዳር 21 ቀን 1971 ዓ. ም. በዋለው ችሎት በነጻ ተለቋል ። ይህን ሁኔታ በአሁኑ ጉዳይ ውሳኔ የሰጠው ችሎትም በሚገባ ያውቀዋል ። ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ በድምጽ ብልጫ የተሰጠው ውሳኔ « እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹሕ ነኝ የሚል ሰው ይህን ወንጀል እስከመሥራትና እስከማሠራት ያደረሰው ምንድነው? የሚል ጥያቄ እስካሁን መልስ ያልተገኘለት ቢሆንምቅሉ ፣ በበኩላችን ግን ያሳዛኙ የኃ. ፀ. የግፍ አገዳደል ወንጀል እንቅቅልሽ ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ የታቀደ ዘዴ ሳይሆን አይቀርም የሚል እምነት እንድናሳድር የነገሩ አካባቢ ያስገደደን መሆኑን ሳንገልጽ አናልፍም » የሚል ትችት ሠንዝሯል ። ይህ ትችት የተሠነዘረው አንደኛው ይግባኝ ባይ በተከሰሰበት የሰው መግደል ወንጀል በነጻ ከተለቀቀ ከአሥራ አንድ ወራት በኋላ ነው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በአንድ በኩል አንደኛው ይግባኝ ባይ የአሁኑን ወንጀል ለምን እንደፈጸመው በውል ተለይቶ አለመታወቁን ይገልጥና በሌላ በኩል ደግሞ ነጻነቱ በአደባባይ የተረጋገጠለትን ሰው ተከሶ ነጻ የወጣበትን ወንጀል ለማዳፈን ነው የሚል መልስ ይሰጠናል ። እዚህም መደምደሚያ የደረሰው በግዙፍ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ሳይሆን በግል ያሳደረውን ጥርጣሬና እምነት መሠረት በማድረግ ነው ። ዳኛ ደግሞ ይህ ያደርግ ዘንድ አይገባውም ። «እንደ ጲላጦስ ንጹሕ ነኝ» ፤ «ያሳዛኙ የኃ. የግፍ አገዳደል» የሚሉት ስሜታዊ ቃላት ጉዳዩ በገለልተኝኛነት እንዳልታየ በጉልህ የሚያረጋግጡ ናቸው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በዚህ አድራጐቱ ግዙፍ በሆነው ፍሬ ነገር ሳይሆን በስሜት ተመርቷል ። ገለልተኛነቱን ሠርዞታል ። የዳኝነትን መሠረታዊ አቋም ንዶታል ። በመጨረሻም የድምጽ ብልጫው ውሳኔ« ያም ሆነ ይህ የቀረበልን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የማያሻማና አጥጋቢ ስለሆነ » ተከሳሹቹ ጥፋተኞች ናቸው ሲል አስተያየቱን ይደመድማል ። የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የማያሻማና አጥጋቢ ከሆነ የታወቀ የሕግ ተመራማሪዎች የነደፉትን አሳብ ቦታ ሳይሰጡ በመጠቀስ ብቻ በድብደባ የተገኘ የአንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃል ብቁና ሐቀኛ ነው በማለት የማይታመነውን ለማሳመን ያ ሁሉ መከራ ለምን አስፈለገ? የታወቁት ሊቃውንት እነ እርችቦልድና ሾው አንድ የእምነት ቃል በሌላ የእምነት ቃልና አካባቢ ማስረጃ ተደግፎ ሲገኝ ሙሉ እምነት ሊጣልበት ይገባል ያሉትን የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ደጋፊ አሳብ ነው ብሎ ጠቅሶታል ። ነገር ግን ንድፈ አሳቡን ለውርደበጅ ያህል ጠቀሰው እንጂ ከቀረበለት ጉዳይ ጋር አላዛመደውም ፣ አላዋሃደውም ። ይህን ቢያደርግ ኖሮ የጠቀሳቸው የሕግ ምሁራን የነደፉት አሳብ እርሱ ከደረሰበት መደምደሚያ ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑን ይረዳው ነበር ። የተጠቀሱት ሊቃውንት የእምነት ቃል ብቻውን ብቁና አስተማማኝ ነው አላሉም ። እነርሱ ያሉት አንድ የእምነት ቃል በሌላ የእምነት ቃልና የአካባቢ ማስረጃ ከተደገፈ ሊታመን ይገባል ነው ። እኛም በዚህ አሳብ እንስማማበታለን ። በያዝነው ጉዳይ ግን የቀረበው ተከሳሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጡ የተባለው የእምነት ቃል ብቻ ነው ። ይህን የእምነት ቃል የሚያጠነክር አንዳችም የአካባቢ ማስረጃ አልቀረበም ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ የሊቃውንቱ ንድፈ አሳብ ምን ለማሳመን እንደተጠቀሰ አልገባንም ።

እንግዲህ ነገሩን ስናጠቃልለው ይግባኝ ባዮቹ ፈጸሙ ለተባሉት ወንጀል የቀረበባቸው በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል ብቻ ነው። ተከሳሾቹ ግን ጉዳዩ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የተነገረባቸውን ድርጊት መፈጸማቸውን ክደውታል ። በፖሊስ ጣቢያ ማመናቸውን ባይክዱም ፥ ይህን የእምነት ቃል የሰጡት ወደውና ፈቅደው ሳይሆን ከባድ የድብደባ ተግባር ስለተፈጸመባቸው ሥቃዩን መቋቋም ስላቃታቸው መሆኑን ገልጠው ማስረጃነቱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ። ለምርመራ ፖሊስ ጣቢያ በነበሩበት ጊዜ በተከታታይ ለአራት ቀናት ተደብድበውና ቆስለውም እንደነበረ የቆጠሯቸው የመከላከያ ምስክሮች በሚገባ አስረድተውላቸዋል ። በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንድ ተከሣሽ ተጨማሪ አስረጂ ሊሆንበት ይችላል ። ነገር ግን የእምነቱ ቃል ተጨማሪ አስረጂ የሚሆነው ተከሳሹ ያላንዳች ተጽእኖ ፡ ማስፈራራትና ማግባባት በንጹህ ኅሊና በራሱ ፈቃድ የሰጠው ከሆነ ነው ። በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ባዮቹ ለምርመራ ፖሊስ ጣቢያ በነበሩበት ጊዜ በከባድ ሁኔታ ተደብድበው እንደነበረ በመከላከያ አስረጂዎች ተረጋግጧል ። የተደበደቡ መሆናቸው ከተረጋገጠ ደግሞ የእምነቱን ቃል ወደውና ፈቅደው ሰጥተውታል ለማለት አይቻልም ። ይግባኝ ባዮቹ ድርጊቱን መፈጸማቸውን ያላንዳች ማስገደድ በራሳቸው ፈቃድ በፖሊስ ጣቢያ ካመኑ ፥ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ የሚክዱበት ምክንያት አይታየንም ። አስቀድመው ለማመን ፈልገው በኋላ አሳባቸውን ለውጠው ክደውታል እንጂ በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል ትክክል ነው እንዳይባል ፥ ይህን መደምደሚያ የሚያጠናክር ተጨማሪ ግዙፍ ማስረጃ አልቀረበም ። ይግባኝ ባዮቹ ወንጀሉን ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩት ምን ፍንጭ ተገኝቶ ወይም በማን ተጠቁሞ እንደሆነ በጭራሽ የሚታወቅ ነገር የለም ። በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል የኃይል ተግባር ተፈጽሞባቸው የተገኘ መሆኑ እየተረጋገጠና የኃይል ተግባር ቢፈጸምባቸውም የሰጡት የእምነት ቃል ትክክል ነው ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት ተጨማሪ ግዙፍ ማስረጃ ሳይቀርብ ይግባኝ ባዮቹ ጥፋተኞች ሊሆኑና ሊቀጡ አይገባቸውም ። ስለዚህ ከፍተኛው ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ የሰጠውን ፍርድ ሠርዘንና አነስተኛውን ድምጽ ደግፈን ይግባኝ ባዮቹን በነፃ አሰናብተናቸዋል ። ፍርዱ መሻሩን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይተላለፍለት ፡ እንዲሁም ይግባኝ ባዮቹን እንዲለቃቸው ታስረው ለሚገኙበት ወህኒ ቤት ይጻፍለት ብለናል ።

# ተገዶ ክስን ስለማመን—በወንጀል ይግባኝ

## መ. ቁ. 4/71 የፍርድ ጉዳይ ትችት ።

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር*

በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የመረመረው ጭብጥ ተገዶ ክስን ማመንን የሚመለከት ነው ። በዚህ ጉዳይ የተነሱ ጭብጦች ፤

ሀ/ በማስገደድ የሚገኝ የእምነት ቃልን በማስረጃነት ለመቀበል አስተማማኝና የማያስተማምን በማለት ልዩነት መፍጠር ይገባል ? ወይስ

ለ/ በማስረጃነት የቀረበው የእምነት ቃል በማስገደድ የተገኘ መሆኑን በመመልከት ብቻ አስተማማኝ ቢሆንም ባይሆንም ተቀባይነት ማጣት አለበት ? የሚሉት ናቸው ።

አንድ ሰው ወንጀል ስለመሥራቱ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ባለው በማያጠራጥር ማስረጃ መረጋገጥ አለበት[1] የሚለው ሕጋዊ አቋም ተቀባይነት ያገኘው ከብዙ የታሪክ ሂደት በኋላ ነው ።

በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ንጹህነታቸውን ለማረጋገጥ ከወነጀሏቸው ሰዎች ጋር ፍልሚያ ገጥመው ማሸነፍ አለባቸው ይባል የነበረበት ዘመን ነበር ።[2]

አሁን ባለንበት ዘመን ምንም እንኳን በኃይል በማስፈራራት ወይም በሌላ ሕገ ወጥ ዘዴ መጠቀም በሕግ መከልከሉ ተገቢ ነው ብሎ በማለት የተለያዩ መርሆዎችን መጥቀስ ቢቻልም ፤[3] ከማስረጃ ሕግ አንጻር ስናየው ግን ማንም ሰው ጥፋተኛነቱ እስካልተረጋገጠበት ድረስ እንደ ንጹህ ይቆጠራል ከሚለው መርህ ጋር የተሳሰረ ሆኖ እናገኘዋለን ።

አንድ ሰው ጥፋተኛነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ንጹሕ ነው ብሎ መገመት በሁሉም አገር ተቀባይነት ያገኘ መርህ ለመሆኑ ከተለያዩ ጽሁፎች ፣ ስምምነቶችና የሕግ ቅንጅቶች ማየት ይቻላል ። በዚሁም መሠረት በዲሴምበር 16/1966 ዓ. ም. በወጣው ዓለም አቀፍ የፍትሐብሔርና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 2 « ማንም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በሕጉ መሠረት ወንጀለኛነቱ እስኪረጋገጥበት ድረስ እንደንጹህ የመገመት መብት ይኖረዋል »[4] ተብሎ ተደንግጓል ። ሩዶልፍ ሄርማን የተባለው ምሁር « በምንም ዓይነት መንገድ ጥርጣሬ ብቻውን እንደበቂ ምክንያት ተወስዶ ማንኛውም ሰው ሕግ አክባሪ ዜጋ ነው የሚለውን መሠረታዊ እምነት ሊያስለውጥ አይገባም » በማለት ጽፏል ።[5] በሶቭየት ሕብረትና በዩንየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርህ በክፍል 14 በፓራግፍ ሁለትና ሶስት የሚከተለው ተደንግጎ ይገኛል ፤ « ፍ/ቤቱ ፣ ዐቃቤ ሕጉ ፣ መርማሪውና ቃል ተቀባዩ ምን ጊዜም ቢሆን የማስረዳቱን ሸክም ወደ ተከሳሽ ሊያዞሩ አይችሉም ። በኃይል በመጠቀም ፣ በማስፈራራት ፣ ወይም በሌላ ሕገወጥ ዘዴ በመጠቀም ከተከሳሹ ማስረጃ ማግኘት የተከለከለ ነው ። »[6]

እነዚህ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች « ከወንጀል ምርመራ ጋር አግባብ ያላቸው ተቋሞች ሁሉ አንድን ሰው በቅድሚያ እንደጥፋተኛ መገመት እንደሌላባቸውና ምን ጊዜም ፍርድ መስጠት የሚገባቸው በግልጽ በሚታይና በማይታብል ማስረጃ መሠረት መሆን እንዳለለበት ያስገነዝባሉ ። »[7]

ከላይ ከተገለጸው መገንዘብ እንደሚቻለው እንደ ንጹህ መገመት የሚለው መርህ የተከሳሹ ጥፋተኛነት በሚገባ የሚያስጠረጥር ማስረጃ ከመገኘቱ በፊት ጥፋቱን የማስረዳት ሕግን ማስፈጸም ተግባራቸው ከሆነው ተቋሞች ወደ ተከሳሹ መዞር እንደሌለበት ይደነግጋል ። በሶቭየት ሕብረትና በዩንየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎች የአንድ ተከሳሽ እንደ ንጹህ የመገመቱ መብት በተግባር መተርጐም የሚጀምረው ገና ምርመራው ከሚጀምርበት ጊዜ እንስቶ ለመሆኑም ከላይ ከተጠቀሰው መረዳት ይቻላል ። ይህ እንግዲህ በተጨባጭ በተግባር ሲተረጉም ማንም መርማሪ ባለሥልጣን አንድን ሰው ተጠርጣሪ ነው ብሎ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል አስጨናቂ በሆነው ምርመራ እንዲጠመድ ከማድረጉ በፊት ያንን ሰው በበቂ ምክንያት ለመጠርጠር የሚያስችሉ ማስረጃዎች በተጠርጣሪው አማካይነት ሳይሆን በቴክኒካዊ ምርመራ በቅድሚያ መሰብሰብ አለበት ማለት ነው ።

ቢሆንም ወንጀለኞችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ሕብረተሰቡን ከወንጀል ድርጊቶች የመከላከል ከባድ ኃላፊነት የተጣለባቸው ፖሊሶች በሶቭየት ሕብረትና በዩንየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎች ክፍል 14 አንቀጽ ሁለትና ሶስት አገላለጽ መሠረት « ማስረጃውን ወደ ተከሳሽ የማዞሩን » ክልከላ እና « ማስረጃ ለማግኘት በኃይል ፥ በማስፈራራትና በሌላም ሕገወጥ ዘዴ » ያለመጠቀምን ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ ሆኖ ያገኙታል ።

ይህንኑ ችግር በመረዳት ፖሊሶች በስልጣናቸው ያላግባብ በመጠቀም ወንጀለኛነቱ ያልተረጋገጠበትን ተከሳሽ እንደ ንጹህ ሰው የመገመት መብቱን እንዳይገፉት ለመከላከል የተለያዩ አገሮች የተለያዩ ዘዴዎችን በመቀየስ በሕጋቸው አሥፍረው ይታያሉ ።

ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር ይህ « ያለአግባብ » በስልጣን መጠቀም « ተከሳሹ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር በነበረበት ጊዜ የተጠረጠረበትን ጥፋት በማስመልከት የሚደረገውን ጥያቄ ሁሉ በማስረጃነት እንዳይቀርብ በመከልከል ችግሩ ይቃለላል ተብሎ ይታመናል ። »[8] ከዚህም በላይ ፍርድ ቤቶች ተከሳሹ የሰጠው የእምነት ቃል ራሱን ከወንጀል ነጻ ከሚያደርገው መብት ጋር ተጻራሪ በሆነ መንገድ የተገኘ ከመሰላቸው ማስረጃው ዋጋ እንዳይኖረው ሊያደርጉት ይችላሉ ።[9]

በአሜሪካን አገር ይህ ያለአግባብ በሥልጣን የመጠቀም አዝማሚያ ተጠርጣሪው በፖሊስ ጣቢያ በሚቆይበት ጊዜ ከሕግ አማካሪው ጋር እንዲገናኝ ዕድል በመስጠት ይወገዳል ተብሎ ይገመታል ። ተጠርጣሪው ይህን መብት ከተነፈገ ሰጠው የተባለው የእምነት ቃል ሁሉ የሚታመን ቢሆንም እንኳን በግዴታ እንደተገኘ ተቆጥሮ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም ።[10]

በህንድ አገር ግን አሠራሩ ለየት ያለ ነው ። በተከሳሽ የተሰጠ የእምነት ቃል በማስረጃነት ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ በመርማሪ ዳኛ (ማጅስትሬት) ፊት መሰጠት አለበት ። ይህ አሠራር የእምነቱ ቃል የተሰጠው በፈቃደኛነት ነው ብሎ ለማመን ያስችላል ተብሎ ይገመታል ። [11]

በዩጎዝላቪያ ደግሞ ከነዚህ የተለየ አሠራር ይታያል ። ከሜይ 11 ፥1967 ዓ. ም. በፊት በዩጎዝላቪያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት የመመ ርመር ሥልጣን የተሰጣቸው ሁለት ተቋሞች ነበሩ ። እነርሱም ፖሊስ እና ፍርድ ቤት ነበሩ ። ሆኖም ሜይ 11 ፥ 1967 ዓ. ም. በወጣው ሕግ መሠረት ሙሉ በሙሉ በፖሊስ ይካሄድ የነበረው ምርመራ እንዲቀር ተደርጓል ። አሁን የሚሠራ በት የምርመራ ዓይነት ራሱ « ዋናው ምርመራ » ሲሆን ይህም ሙሉ በሙሉ በዳኛ ይካሄዳል ።[12] በተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት አዲሱ የፖሊስ ተግባር « ለዐቃቤ ሕጉ መነሻ የሚሆን ማስረጃ ማጠናቀር ሲሆን ይህም ዐቃቤ ሕግ በምርመራው ይገፋበት ወይም ይተወው እንደሆን ለመወሰን ያስችለዋል እንግዲህ የሕግ አውጪው ዓላማ ፖሊስ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ቢሆን ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል በማስመልከት ጥያቄ በማ ድረግ ማስረጃ እንዳያቀርብ መሆኑ ግልጽ ነው ። »[13] ለዚህ ዓይነቱ አሠራር መፈ ጠር ዋና ምክንያት የሆነው በፖሊሶች በኩል የሚታየው የሰዎችን በንጹህነት የመ ገመትን መርህ በትክክል ሥራ ላይ ያለማዋል ይመስላል ።[14]

እንደ ንጹህ የመገመት መርህ በኛም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ከመጀመሪያው የምርመራ ደረጃ ጀምሮ ይገኛል ። አንድን ግለሰብ ከሌሎች ሁሉ ነጥሎ ወንጀሉን የፈጸመው እርሱ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ዓይን ሳይጣልበት በፊት መርማሪው ፖሊስ ለጥርጣሬው መነሻ የሚሆነው በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገ ባል ።[15] ከዚህም በላይ ፥ « ፖሊሱ የምስክርነት ቃል ሲቀበል ተጠያቂውን መደለል የተስፋ ቃል መስጠት ፥ የማስፈራራት ፥ የኃይል ሥራ ወይም ሌሎች ከሕግ ውጪ የሆኑ ዘዴዎች መፈጸም አይችልም »[16] ተብሎ ተደንግጓል ።

አንድን ወንጀል መመርመር ተግባሩ የሆነ ፖሊስ ይህን ተግባሩን በሚያከና ውንበት ጊዜ ተመርማሪውን በመደለል ፥ በማስፈራራት ፥ የተስፋ ቃል በመስጠት ወይንም በሌላ ተገቢ ባልሆነ ዘዴ በመጠቀም ተመርማሪው ቃል እንዲሰጠው ያደ ረገ እንደሆነ ቅጣት እንደሚያገኘው በሕጋችን በግልጽ ተደንግጓል ። የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/1974 ዓ. ም. አንቀጽ 22 እንደሚ ከተለው ይደነግጋል ፤

« 1. ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ የታዘዘውን ፥ ተይዞ በማረፊያ ቤት ወይም በእ ሥራት የተቀመጠውን ወይም በተለየ ቦታ እንዲቀመጥ የተወሰነበትን ሰው የሚ ጠብቅ የመንግሥት ሹም ወይም ሠራተኛ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ወይም የሕ ብረት ሥራ ማሕበር ተመራጭ ወይም የጥበቃ ጓድ አባል ፤ የተሰጠውን ሥራ በሚ ያከናውንበት ጊዜ ፤ በዚህ ሰው ላይ ከሰብዓዊ ርህራሄ ውጪ የሆነ ወይም ለሰው ልጅ ክብር ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈጸመበት እንደሆነ ፥ ይህ አድራጎቱ ሊያስከት ልበት የሚችለው የከባድ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ... ዕወሳሰን ደንብ ከሌለ እስከ አምስት ዓመት ሊደ ርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል ።

« 2. ወንጀሉ የተፈጸመው በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ባለሥል ጣን ትዕዛዝ ከሆነ ፥ ይኸው ባለሥልጣንም ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል[17] ። »

ነገር ግን ፖሊስ በሕግ ከተደነገገው መንገድ ተጻራሪ በሆነ ዘዴ ከተከሳሹ የእምነት ቃል አግኝቶ በማስረጃነት ሲያቀርብ ፥ በዚህ ዘዴ የተገኘ ማስረጃ በሕግ ምን ያህል ክብደት እንደሚሰጠው በሕጉ አልተደነገገም[18]።

በሌላ በኩል ግን ፍርድ ቤቶች የዚህ ዓይነት በግዴታ የተገኘ ማስረጃ ሲያጋጥማቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሕጉ ሥልጣን ባይሰጣቸውም ፣ በልምድና በሥራቸው ጠባይ ምክንያት ውሳኔ መስጠት ስላለባቸው ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ወይም አይገባም ብለው መወሰን አለባቸው ። በዚህ ጉዳይም ከሞላ ጎደል የተደረገው ይኸው ነበር ።

ጉዳዩ ሲመረመር እንደሚያረጋግጠው እንደ ንጹህ የመገመት መርህና ይህንኑ በተግባር ለመተርጐም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት በቁ25 የተደነገገውን በመከተል ፖሊሶቹ ይግባኝ ባዮቹ ከሰጡት ቃል ሌላ ማስረጃ ለማግኘት ጥረት አላደረጉም። ፖሊሶች ይግባኝ ባዮችን በቁጥጥራቸው ሥር ከማዋላቸው በፊት ይግባኝ ባዮቹን በሚገባ የሚያስጠረጥር በይግባኝ ባዮች ቃል ያልተመሠረተ ማስረጃ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት በማድረግ ፈንታ በስሜታዊ ግፊት ብቻ ቀን ሳስተው ፣ ይግባኝ ባዮቹን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋልና የእምነት ቃላቸውን እንዲሰጡ በማስገደድ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 31 ን ከመጣሳቸውም በላይ የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁ. 21 ንም በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል ። ከዚህም በስተቀር የይግባኝ ባዮቹን የእምነት ቃል እንኳን የሚያጠናክር ተጨማሪ ማስረጃ አላገኙም ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ባዮቹ ተሰጠ የተባለው የእምነት ቃል በፈቃደኝነት የተገኘ ካለመሆኑም ሌላ በአካባቢ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ሳይቀበለው ቀርቷል ። የእምነት ቃሉ በሌላ ተጨማሪ ማስረጃ የተደገፈ ቢሆን ኖሮ ይቀበለው ወይስ አይቀበለውም ነበር ? ስለሚለው ጥያቄ ግን ግምት ከመውሰድ በስተቀር ፍርድ ቤቱ የወሰደው ግልጽ የሆነ አቋም አለ ለማለት ያስቸግራል ።

## መ ደ ም ደ ሚ ያ ።

1. ፍርድ ቤቱ በመሠረቱ የሰጠው ውሳኔ በዚህ ጉዳይ የተገኘው የእምነት ቃል በድብደባ የተገኘ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም የሚል ነው ። ሆኖም በፈቃደኝነት ያልተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት የሚያጣው እምነት የማይጣልበት ሲሆን ነው የሚል ተጨማሪ አስተያየትም ከፍርዱ መውሰድ ይቻላል ።

2. የተሰጠው የእምነት ቃል አስተማማኝ ቢሆንም እንኳ በማስገደድ የተገኘ እስከ ሆነ ድረስ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም ብሎ መወሰን ፖሊሶች በዚህ ዓይነቱ አሠራር እንዳይቀጥሉ ለማድረግ ይረዳል የሚለውን አመለካከት ፍርድ ቤቱ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ያመነበት አይመስልም ። የፍርድ ቤቱ አቋም በምርመራ ጊዜ አስገድዶ የእምነት ቃል መቀበል የሚያስቀጣ አሠራር እንደመሆኑ መጠን ማስረጃው አስተማማኝ ከሆነ ይህን በማስረጃነት ተቀብሎ የእምነት ቃሉን በማስገደድ ያገኘውን ፖሊስ መቅጣት የተሻለ መፍትሔ ነው የሚል ይመስላል ።

3. የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተመሰረተው ፍርድ ቤት በሚነሱት ክርክሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ባለው ሥልጣን እንጂ በሕግ በተደነገገ ሥልጣን አይደለም ። ሆ

ኖም የዳኛ ሥልጣን መመንጨት ያለበት ከተደነገገ ሕግ ነው የሚለውን አመለካከት በመቀበል ሕጐች ሁሉ ተደንግገው በሚወጡበት አገራችን ራሱን የቻለና የተሟላ የማስረጃ ሕግ[19] ያለመኖር ብዙ ችግርን የሚያስከትል ስለሆነ ፡ ይህ በቶሎ መፍትሄ ሊደረግለት የሚገባ ጉዳይ ነው ።

4. የዚህ ዓይነቱ ሥልጣንን የመተላለፍ አዝማሚያ በፖሊስ በኩል የሚታየው ፖሊሶች በኃይል ተጠቅመው አንድን ተጠርጣሪ ማሳመን ልዩ ጥቅምን ያስገኝልናል ብለው ስለሚያምኑ አይደለም ፤ በሕጉ ላይ ንቀት አድሮባቸው ነው ለማለትም አይቻልም ። ምክንያት ሊሆን የሚችለው ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል ተግባራቸው ስለሆነ ማንም ሰው ወንጀለኛነቱ ካልተረጋገጠበት በስተቀር እንደ ንጹሕ ይቆጠራል የሚለውን መርህ የሚተላለፉት በተጠርጣሪ ወንጀለኞች ላይ ባላቸው ከምያ ግዴታቸው በሚመነጭ ስሜታዊ አመለካከት ነው ። [20] ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ከሕግ ውጪ መሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ ብቻ ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ በዩጐዝላቪያ እንደሚደረገው የወንጀል ምርመራን ተግባር ከፖሊስ ክፍል ወስዶ ወደ ዳኝነቱ ክፍል ማስተላለፍ ከጊዜው በጣም የቀደመ አሠራር ሊሆን ይችላል ።
ቢሆንም አሁን ያለውን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 27 ን በማሻሻል ፖሊስ የተከሳሽን ቃል እንዳይቀበል ማድረግና ቀድሞም እንደተባለው[21] ቁ. 35 ን እንዳለ እንዲቀይ ማድረግ ይበጃል ። ይህም ሲሆን በፍርድ ቤቱም ቢሆን የሚሰጠው የእምነት ቃል « ስውር » ተጽዕኖ ወይም ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በፖሊስ የተፈጸመበት የኃይለ ሥራ ያለመኖሩን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ደንቦች መታከል ይኖርባቸዋል ። ይህ ከተሟላ በዚህ ፀሐፊ እምነት ከሥልጣን በማለፍ በሕገወጥ መንገድ የእምነት ቃል የማግኘቱን አሠራር ጨርሶም ባያጠፋው በጣም ይቀንሰዋል ።

---

## የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

* ረዳት ፕሮፌሰር ፡ ሕግ ፋኩልቲ ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ።

1. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 141 ይመለከቷል ።

2. ፕሉስኮው ሞሪስ ፡ ዘ ዲቨሎፕመንት ኦፍ ፕረዘንት ዳይ ክሪሚናል ፕሮሰጀርስ ኢን ኢሮፕ ኤንድ አሜሪካ ፡ ሀርባርድ ሎው ረቪው (ቅጽ 48 ፡ 1934—35) ፤ ገጽ 440 ።

3. ለምሳሌ የፌዴራሊስት ዩጐዝላቪያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 176 ን ብንመለከት እንዲህ ይላል "በሰው ልጅ ክብረ — ሀሊና ፡ የግለሰብም ሆነ የቤተ ሰብ ሕይወት (አኗኗር) እንዲሁም ሌሎችም፤ ሰብአዊ መብቶች ሁሉ የተጠበቁ ናቸው ።

"በኃይል በመጠቀም የእምነት ቃልም ሆነ ምስክርነት ማግኘት የተከለከለ እና የሚያስቀጣ ነው ።" እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው በኃይል በመጠቀም የእምነት ቃል ማግኘት በሰብአዊ ክብረ—ሀሊና ላይ ወንጀል መፈጸም መሆኑን ነው ። እንዲሁም ዊግሞር ፡ ኤቪደንስ ኢን ትራያልስ አት ኮመን ሎው (ሊትል ብራውንና ኩባንያው እ.ኤ.አ. 1970) ቅጽ 3 ፡ ገጽ 329—344 ይመለከቷል ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በኃይል የተገኘ የእምነት ቃል ማስረጃነቱ የማያስተማምን ከመሆኑም በላይ በራስ ላይ ምስክር ከመሆን ነጻ የሚያደርገውን መብት ይጻረራል ተብሏል ። ቢሆንም የኋለኛው ቲኦሪ አንድ ሰው ወንጀለኛነቱ ካልተረጋገጠበት በስተቀር እንደ ንጹህ ሰው ይቆጠራል ከሚለው መርህ ጋር አንድ አካል ነው ። ምክንያቱም ይህ አባባል ራሱ አንድ ሰው በወንጀለኛነት ተጠርጥሮ ከሌሎች ሕግ አክባሪ ሰዎች መካከል ተነጥሎ ከመውጣቱ በፊት ያለእርሱ እርዳታ በቅድሚያ ወንጀለኛነቱን የሚያመለክት ማስረጃ መሰብሰብ እንደሚገባው ስለሚያሳይ ነው ።

4. ሄርማን ጂ. ዲ. አር ክሪሚናል ፕሮሲጀር ሎው ጎቨርንድ ባይ ሶሻሊስት ፕራንስፕልስ፣ ሎው ኤንድ ሌጂስለሽን ኢን ዘ ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ (እ.ኤ.አ. 1974፤ሁለተኛ እትም) ገጽ 29።

እንዲሁም ፣ « ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በግልጽ ችሎት ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ጥፋተኛነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥበት ድረስ እንደ ንጹህ ይገመታል » የሚለውን በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማረጋገጫ አንቀጽ 11/ 1 የተደነገገውን በብራውንሊ ፤ ቤዚክ ዶኩመንትስ ኦን ሂዩማን ራይትስ ( ክላሬንደን ፕሬስ ኦክስፎርድ ፣ እ. ኤ. አ. 1971 ) ገጽ 109 ይመለከቷል ። በተለያዩ አገሮች ሕጐች ውስጥ ስለሚገኙ ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ይህንኑ መጽሐፍ፣ ገጽ 3—89 ይመለከቷል ።

5. ሄርማን ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 29 ።

6. ሎው ኢን ኢስተርን ኢሮፕ (ቅጽ 3) ገጽ 119 ላይ የሚገኘውን የሶቪየት ህብረትና የዩንየን ሪፑብሊኮች የወ. መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆች ክፍል 14 ፤ ፓራግራፎች 2 እና 3 ን ይመለከቷል ።

7. ሂርማን ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 19—30

8. ፊሸር ፣ ያለ ነጻ ፈቃድ የሚሰጡ የእምነት ቃላትና የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 35 የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ( ቅጽ 3 ቁ. 1) ገጽ 317 ።

9. ከላይ እንደተጠቀሰው ።

10. ከላይ እንደተጠቀሰው ነገር ግን በድህነት ውስጥ በሚገኙ ሰዎችና በተለይም በከበርቴው ህብረተሰብ « በታችኛው መደብ » አባል ላይ ባለው ዝቅተኛ አመለካከት ምክንያት ይህ መብት ምን ያህል በተግባር ላይ ሊውል እንደሚችል ያጠራጥራል ።

11. ከላይ እንደተጠቀሰው ፣ ገጽ 332 ።

12. ኮሌክሽን አፍ ዩጐዝላቭ ሎውስ ፣ ኮድ ኦፍ ክሪሚናል ፕሮሲጀር (ቢዖግራድ ፤ እ ኤ አ 1969) ቅጽ 19 ፣ ገጽ 9 ።

13. ከላይ እንደተጠቀሰው ። ዳኛ በመጀመሪያው የወንጀል ምርመራ ደረጃ ውስጥ ስለወንጀሉ አፈጻጸም ምርመራ የሚካሄድ ሚና እንዲኖረው የተደረገው አሠራር ከሲቢል ሎው የሕግ ቅንጅት የተገኘ ለመሆኑ ፣ ከላይ በግርግ ማስታወሻ 2 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 433—467 ይመለከቷል ።

14. ከላይ እንደተጠቀሰው ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 ገጽ 8 ይመለከቷል ።

15. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 25

16. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 31

17. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 41ኛ ዓመት ቁ. 2 ። እንዲሁም የወ. መቅጫ ሕግ ቁ. 417ትን ይመለከቷል ።

18. በወ.መ. ሕግ ሥነ ፡ ሥርዓት አዋ ፕሮጀ ድጋሚ ቁ. 462 ንዑስ ቁ. 2 ሥር በፊሸር፡ ኢትዮጵያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኮድ ፣ ኤ ሶርስ ቡክ ( አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ጋር በመተባበር ያሳተመው ፣ እ.ኤ.አ. 1969) በገጽ 458 እንደሚገኘው ሕገ ወጥ በሆነው መንገድ የተገኘ የእምነት ቃል ውጤት እንደማይኖረው ይደነግጋል ። ቢሆንም ይህ ረቂቅ በአሁኑ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን ቁ. 31 ተተክቷል ። እንደፊሸር አባባል (ከላይ በግ. ማስታወሻ ቁ. 8 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 333—34) በወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 31. ስር የእምነት ቃሉ ሊኖረው ስለሚችለው የማስረጃነት ጠባይ ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምናልባት ሕግ አውጪው ይህ በማስረጃ ሕግ ይደነገጋል የሚል እምነት ስለነበረው ይመስላል ።

19. ይህም ሲባል በሕጋችን ውስጥ ማስረጃን የሚመለከት ሕግ የለም ማለት አይደለም ። ለምሳሌ የፍትሐብሔር ሕግ ( ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 19ኛ ዓመት ቁ. 8 አዋጅ ቁ. 165/52) ቁ. 2001—2026 ይመለከቷል ።

20. ፊሸር ፣ ስለ ኢትዮጵያ መያዝ ሕግ አንዳንድ ጉዳዮች ፣ በማጠናቀር ሕግን የማሰናዳት ዘዴ ፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት (ቅጽ 3 ቁ. 2) ገጽ 438 — 439 ።

21. ፊሸር ፣ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 320—329 ይመለከቷል ።